የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺ፰ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.. 20
ADDIS ABABA, 22nd December , 2015

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፷፰/፪ሺ፰ ዓ.ም
የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………..…………………………………..………………..ገጽ ፰ሺ፯፻፳

## CONTENT

Regulation No.368/2015
Ethiopian Agricultural Businesses Corporation Establishment Council of Ministers Regulation…………..……………………………...…………….……page 8720

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፰/፪ሺ፰**

## የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፰/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**COUNCIL OF MINISTER REGULATION No. 368/2015**

## COUNCIL OF MINISTER REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN AGRICULTURAL BUSINESSES CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 47(1) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Agricultural Businesses Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 368/2015".

2. **Establishment**

1/ The Ethiopian Agricultural Businesses Corporation (hereinafter the "corporation") is hereby established as a Federal Government public Enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

፫. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**
የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**
የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**
ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር ገዝቶ ለገበያ ማቅረብ፣ ማዘጋጀት፤ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችን የገበያ ዋጋ የማረጋጋት ተግባራትን ማከናወን፤

፪/ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት፣ የእርሻና የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን የጥገና አገልግሎት፣ የእርሻ መሣሪያዎችንና የትራንስፖርት ተሽከርካሪ ዎችን የኪራይ አገልግሎት በክፍያ መስጠት፤

፫/ የእርሻ መሣሪያዎችንና መለዋወጫዎችን፣ የኮንስት ራክሽን መሣሪያዎችን እና አግሮ ኬሚካሎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር ገዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ፤

፬/ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች አጠቃቀም እንዲለመድ አስፈላጊውን ትምህርት መስጠት፤ ስለእርሻ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም የምክር አገልግሎት መስጠት፤ የቴክኒክ ሙያ ማሻሻያ ሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤

፭/ የተፈጥሮ ሙጫ ምርት መሰብሰብ፣ መግዛት፣ እሴት መጨመር፣ ማዘጋጀት፤ ሌሎች ከደን ውጤቶች የሚመረቱ ምርቶችን ማምረት፣ ለሀገር ውስጥና ለውጪ ገበያዎች ማቅረብ፤

3. **Supervising Authority**
The Ministry of Public Enterprises shall be the supervising authority of the Corporation.

4. **Head Office**
The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branches elsewhere in other parts of the country, as may be necessary.

5. **Purposes**
The purpose for which the Corporation is established are:

1/ to buy from domestic and international markets and supply agricultural inputs, process same; undertake agricultural inputs market price stabilization activities;

2/ to render agricultural mechanization services, agricultural and construction equipment repair services and provide rental services of agricultural machineries and transport vehicles;

3/ to buy from domestic and international markets and supply agricultural machineries and spare parts, construction equipment and agro-chemicals;

4/ to provide necessary education for the promotion of the use of modern agricultural machineries; provide consultancy service in handling and use of agricultural machineries and provide on the job technical trainings;

5/ to harvest, buy, value add to and process natural gum, produce other forest products, and supply to domestic and international markets;

፮/ የእርሻ መሬት ልማት ጥናትና ዲዛይን፣ የእርሻ መሬት ቅየሳ፣ ምንጣሮና ማስተካከል፣ የውኃ ተፋሰስና የመስኖ ሥራ እንዲሁም ከእርሻ መሬት ልማት ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን ማከናወን፤

፯/ የአዳዲስና ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አዋጪነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና የኮሚሽኒንግ እንዲሁም የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤

፰/ አቅሙ ካላቸው የአገር ውስጥ እና የውጪ ኩባንያዎች ጋር በመተባበር የግብርና የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና የማምረት ሥራዎች በአገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤

፱/ ለመስኩ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት የምርምርና የሥልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር መሥራት፤

፲/ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመሥረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አስተዳደር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለውን (ኢንቨስትመንት መሳብንም ሆነ በኢንቨስትመንት መሳተፍን ጨምሮ) ጥናት በማካሄድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲፩/ የተለያዩ የአዝዕርት፣ የአትክልት፣ የፍራፍሬና የመሳሰሉት ቅድመ መሥራች፣ መሥራችና የተመሠከረለት ዘር ማባዛት፣ ማበጠርና ማዘጋጀት፣ እንደአስፈላጊነቱም ቅድመ መሥራች ዘሮችን ከውጭ አገር በማስመጣት ማስመረት ወይም መሸጥ፣ ተረፈ ምርቶችን ለገበያ ማቅረብ፤

6/ to undertake agricultural land development studies and preparation of designs, agricultural land surveying, clearing, leveling, drainage and irrigation activities as well as other activities related to agricultural land development;

7/ to cause undertaking of feasibility studies, design preparation, technology selection and negotiation, erection and commissioning of new and expansion projects as well as for research activities;

8/ to cause the local designing and manufacturing of agricultural machineries and spare parts in partnership with capable local and foreign companies;

9/ to work in cooperation with the concerned educational research and training institutions in producing trained manpower in such fields, numbers and quality as required by the sector;

10/ to undertake studies, based on direction given to it by the Ministry of Public Enterprises, for the acquisition of financial, technological and modern governance inputs (including attracting investments or participating in investments) that can help it to become competitive, both locally and globally, and profitable and implement same upon approval;

11/ to multiply, clean and process pre-basic, basic and certified seeds of various crops, vegetables and fruits; where necessary import pre-basic seeds and cause their production or sale them; to sell byproducts;

፲፪/ በግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ በእርሻ መሣሪያዎች አቅርቦት፣ በእርሻ መሣሪያዎች ጥገና፣ በተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ በሜካናይዜሽን አገልግሎትና በተዛማጅ ሥራዎች ዙሪያ ምርምር በማካሄድ የተሻሻሉትን ተግባራዊ ማድረግ፣ በውጤቱም ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፤

፲፫/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሠጠው አቅጣጫ መሠረት ቦንድ መሸጥ፣ ዋስትና ማስያዝ፣ ከሀገር ውስጥና ከውጪ የገንዘብ ምንጮች የብድር ውል መደራደርና ሲፈቀድ መፈራረም፤

፲፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

## ፮.<u>ካፒታል</u>

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፪ ቢሊዮን ፬፻፵ ሚሊዮን (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ሚሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፮፻፲ ሚሊዮን (ስድስት መቶ አስር ሚሊዮን) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

## ፯.<u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ፰.<u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

## ፱.<u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የሚከተሉት ደንቦች በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡-

፩/ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፬/፲፱፻፹፭፤

፪/ የተፈጥሮ ሙጫ ምርትና ገበያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፱/፲፱፻፹፮፤

፫/ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፯/፲፱፻፹፮፤

12/ to undertake research and implement improvements with respect to the supply of agricultural inputs, agricultural machineries repair, the production and marketing of natural gum, mechanization services and related matters and thereby ensure its competitiveness;

13/ to sell bonds, collateralize, negotiate and sign loan agreements with local and foreign sources in accordance with directives issued by the Ministry of Finance and Economic Corporation and on the basis of the guidance of Ministry of Public Enterprise;

14/ to engage in other related activities for the attainment of its purposes.

## 6. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Corporation is Birr 2,440,000,000 Billion (Two Billion Four Hundred Forty Million) of which Birr 610,000,000 (Six Hundred Ten Million) is paid up in cash and in kind.

## 7. <u>Liability</u>

The Corporation shall not be held liable beyond its total assets.

## 8. <u>Duration</u>

The Corporation is established for an in definite duration.

## 9. <u>Repealed Regulations</u>

The following regulations are hereby repealed:

1/ the Ethiopian Seeds Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 154/1993;

2/ the Natural Gum Processing and Marketing Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 179/1994;

3/ the Agricultural Inputs Supply Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 177/1994;

፬/ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፯/፲፱፻፹፯፣

**፲. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>**

የሚከተሉት የመንግስት የልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ተላልፈዋል፦

፩/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፬/፲፱፻፹፫፣ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት፤

፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፱/፲፱፻፹፯ ተቋቁሞ የነበረው የተፈጥሮ ሙጫ ምርት ገበያ ድርጅት፤

፫/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፯/፲፱፻፹፯ ተቋቁሞ የነበረው የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት፤

፬/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ተቋቁሞ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር ፩፻፵፮/፲፱፻፺፩ አንቀጽ ፭ መሠረት ጥር ፩/፱፻፺፬ እንደ አዲስ ወደ አክሲዮን ማህበርነት ተለውጦ የነበረው የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር፤

፭/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፯/፲፱፻፹፯ ተቋቁሞ የነበረው የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ድርጅት፡፡

**፲፩.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስቴር**

4/ the Agricultural Mechanization Services Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 97/1994.

10. **<u>Transfer of Rights and Liabilities</u>**

The rights and liabilities of the following public enterprises are hereby transferred to the Corporation:

1/ the Ethiopian Seeds Enterprise Established under the Council of Ministers Regulations No. 154/1993;

2/ the Natural Gum Processing and Marketing Enterprise Established under the Council of Ministers Regulations No. 179/1994;

3/ the Agricultural Inputs Supply Enterprise Established under the Council of Ministers Regulations No. 177/1994;

4/ the Agricultural Equipment and Technical Services Enterprise Established under the Council of Ministers Regulation and subsequently converted into a share company as of January 10, 2002 by the Proclamation No. 146/1998 Article 5;

5/ the Agricultural Mechanization Services Enterprise Established under the Council of Ministers Regulations No. 97/1994.

**11. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of December, 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**